# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)

# The Ethiopian Federal Democratic Unity Forum

## የ20 ዓመቱ የኢህአዴግ የምርጫ ሥልታዊ ሴራና ተንኮል ክፉኛ ተጋለጠ! የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድንም ይህንኑ ዳግመኛ አረጋገጠ!

### ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተሰጠ መግለጫ

የደርግ ሥርዓት ወድቆ ኢህአዴግ መንግሥት ሲመሰርት፣ የዓለም አቀፉን ለጋሽ መንግሥታትና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አመኔታ አገኝባቸዋለሁ በማለት ካነገባቸው ሥልቶች መሀከል አንደኛው ምርጫዎችን ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ ሥልቱ በሀገሪቱ መድረብለ ፓርቲ ዴሞክራሲን እያስፋፋ ለመሆኑ መተማመኛ ተደርጎ እንዲወሰድለት እቅድ አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በዚህ ወቅት ጠብቆ የሚያካሂዳቸው ምርጫዎች ሀቀኝነትና ተዓማኒነት ጉዳይ ግን ፈጽሞ ከቁም ነገር የሚገባ አይለም፡፡ ዋና ዓላማው የምርጫን ተውኔት አካሂዶ ሁሌም ‹አሸነፍኩ ፣ ሕዝብ መረጠኝ ወዘተ› በማለት በዴሞክራሲ ሥም ሥልጣን ላይ መቆየት ነው፡፡ ለዚህ የምርጫ ድራማ ማከናወኛ ኢህአዴግ በብዙ ሚሊየኖች የሚቆጠር የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ሲያባክን ኖሯል፣ የውጭ እርዳታም ያለገደብ ሲያጋብስና የሀገሪቱንም ባለሀብቶች ለዚሁ ዓላማ እንዲያዋጡ ሱያስገድድና ተጽእኖ ሲያሳርፍባቸውም ኖሯል፡፡ ይህ ኢህአዴግ ሥልጣን ከጨበጠበት ጉዜ አንስቶ ሲያከናውነው የነበረው የምርጫ ተብዬ ክንዋኔ የዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ እንደሆነ ለማስመሰል በየወቅቱ ብዙ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መዝዞ እያወጣ ለክንዋኔው ተዓማኒነት ማረጋገጫ ይሆኑልኛል ከሚል ታሳቢ በመነሳት ተግባር ላይ እንደሚያውላቸው ያውጃል፡፡ ከነዚህ መሀከል አንዱ የዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን ጋብዞ የነሱን ምስክርነት ለማገኘት መሞከር ነው፡፡ ይህንን ሲያደርግ የኢህአዴግ ዋና ታሳቢው የዓለም አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ማሕበረሰቡን በራሱ ጨዋታ ለመርታት አቅዶ ነው፡፡ ይኸውም ታዛቢውን አካላት ፈርጀ ብዙ በሆኑ ሥልቶች በመተብተብ የምርጫ ተብዬውን ትክክለኛ ይዘት እንዳይዘግቡ በመገደብ ለእርሱ ተዓማኒነት የሚጨምር የተሳሳተ ምስክርነት እደሰጡ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም የውጭ ሀገር ታዛቢዎችን ለማሳሳት የዘረጋውን ትብትብ ሰብረው የሂደቱን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች ይፋ ከሚያደርጉ ታዛቢዎች ጋር ገና ከጅምሩ በ1984 ዓ.ም ከተካሄደው የአካባቢ ምርጫዎች ወቅት ጀምሮ ዘወትር አተካራ መግጠሙ የተለመደ መገለጫው ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለማስታወስ ያህል፣ በ1984 ዓም ምርጫን ለመታዘብ የመጡትን የአሜሪካንና የጀርመን ሀገር መንግሥታዊ ያልሆኑ የዴሞክራሲና መብት ተሟጋች ድርጅቶችን፣ በ1997 ዓም ደገሞ NDI እና IRI የሚባሉ የአሜሪካን የዴሞክራሲ አስፋፊ ድርጅቶችን ከሀገር በማባረር ምርጫውን የመታዘብ እቅዳቸውን ማክሸፍ የሚታወስ ነው፡፡ እንደዚሁም የሚጣለባቸውን ማዕቀቦችና በተለያየ መልክ የሚቀርብባቸውን ተጽእኖዎች አሸንፈው በመቆየት በምርጫው ላይ የታዘቡትን ሪፖርት ያቀረቡት ደግሞ ለዘለፋና ለከፍተኛ

የማጥላላት እንቅስቃሴ መዳረጋቸው የኢህአዴግ የተለመደ ተግባር መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡

እንግዲህ ኢህአዴግ በአንድ ወገን ‹ምርጫዎችን ወቅታቸውን ጠብቄ እያካሄድኩ ስለሆነ መንግሥቴ ዴሞክራሲያዊ ነው› በማለት አጀንዳውን ማራመድ እየፈለገ፣ በሌላ ወገኑ ደግሞ የአንድ ምርጫ ተአማኒነት ማርጋገጫ የሆነውን የሀገር ውስጥ እና የዓለም አቀፍ ገለልተኛ ታዛቢዎች መኖርን ግን እንደ ጦር ይፈራዋል፡፡ ባጭሩ፣ የመንግሥትን ሥልጣን ለብቻው ለመቆጣጠሩ ምክንያታዊነት ምርጫን ይፈልገዋል፣ ሆኖም በሕዝቡ ውሳኔ ከሥልጣን ተገፍትሮ እንዳይወርድ ደግሞ ‹አሸንፌአለሁ› ለማለት የሚያበቃውን ሕገ-ወጥ እርምጃዎች ሁሉ በምርጫዎቹ ሂደት ላይ መወሰድ ይፈልጋል፡፡ ገለልተኛ ታዛቢዎችን አምርሮ የሚፈራቸውም እነዚህ ሕገ-ወጥ እርምጃዎቹ እንዳይጋለጡበት መሆኑ ገሀድ የወጣ እውነታ ነው፡፡ ሌላው የኢህአዴግ ምኞት ለሚያራምዳቸው የምርጫ ድራማዎች ትክክለኛነትና ተዓማኒነት ምስክሮች መፈለጉ ነው፡፡ ለዚህም ዓለማው ይሆኑኛል የሚላቸውን ማዘጋጀቱና አግብብቶና ለመኖም ቢሆን በታዛቢነት እንዲሳተፉ ማድረጉም የተለመደ ስልት ነው፡፡ ይህ እቅዱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተሳክቶለታል፡፡ ለዚህም ስኬቱ ዘወትር በምርጫ ታዛቢነት የሚሰማራው የአፍሪካ ሕብረት ታዛቢ ቡድን አንዱ ሲሆን ከሀገር ውስጥ ደግሞ በ2002 ምርጫ ለታዛቢነት የተቀናጀው የኢትዮጵያ ሲቪክ ማህበረሰቦች ኮንሴርቴዩም የሚባለው አፍቃሪ -ኢህአዴግ ስብስብ ጎልቶ የወጣ ማሳያ ነው፡፡

የአውሮፓ ሕዝብረት ታዛቢ ቡድን የ2002 ዓም ሀገር-አቀፍ ምርጫን እንዲታዘብ ለማብቃት ከፍተኛ ድርድር በኢህአዴግና በአውሮፓ ሕብረት መሀከል ተደርጎ እንደነበር ይታወቃል፡፡ መድረክ የ2002 ምርጫን የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ብቃት ያላቸው ገለልተኛ ታዛቢዎች ካለምንም ተጽእኖ እንዲታዘቡት ከፍተኛ ትግል አድርጓል፡፡ የዚህ ትግሉ አጀንዳ አንዱ የነበረው የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎች ተሳትፎ ጉደይ ነበር፡፡ ስለሆነም የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ስምሪት ሲጀመር አንስቶ ከቡድኑ መሪዎችና ከያንዳንዱ ታዛቢ ንዑስ ቡድን ጋር ግንኙነት በመፍጠር ተልእኳቸውን ሕገ ወጥ ቅድመ ዝግጅቶች ምንነት፣ ሲፈጽማቸው የነበረውን ሕገ-ወጥ ተግባራትና በመድረኩ እንቅስቃሴዎች ላይ እያደረሰ ያለውን ተጽእኖዎች በሚመለከት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከፍተኛ ሙከራ አድርጓል፡፡ በተለይም ብቃት ያላቸው ገለልተኛ የሀገር ውስጥ ታዛቢ የሲቪክ ማህበረሰብ አካላት ተሳትፎ እንዳያደርጉ በስልታዊ ዘዴ በታገዱበት ሁኔታ በቁጥር አናሳ የሆነው የአውሮፓ ሕብረት ቡድን ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት ስለመቻሉ የነበረንን ጥሪጣሬ ለታዛቢ ቡድኑ ገልፀንለታል፡፡

ሆኖም ግን ወደ የምርጡኝ ቅስቀሳ እንደተገባ እንዳየነውና አሁንም ታዛቢ ቡድኑ ካቀረበው የመጨረሻ ሪፖርት እንደተገነዘብነው፣ ከመነሻው የነበረን ስጋታችን ካለ ምክንያት አልነበረም፡፡ ለምሳሌ፣ በየአካባቢው የተሰማራው የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ንዑስ ቡድን ካረፈበት ከተማ ርቆ በየምርጫ ክልሉ መንቀሳቀስ ያለመቻሉ እና ሲንቀሳቀስም ያለመታየቱ ተጠቃሽ ሲሆን፣ ሌላው አሁን ባቀረበው ሪፖርቱም ላይ የግንዛቤ እጥረት በአንዳንድ መሠታዊ ጉዳዮች ላይ ተስተውሏል፡፡ ከነዚህም መሀከል ጎልቶ የወጣው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን በብቃትና በሙያዊ ተሞክሮ እንዳከናወነው መገለፁና ‹ድክመቶች ቢታዩበትም

መንስኤው በቂ ቁሳዊና የገንዘብ ድጋፍ ያለማግኘቱ ነው› በማለት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ በሚያደርገው ጥረቶችና በሚከፍላቸውም መስዋእትነቶች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ደባ ሲፈፀም፣ ለኢህአዴግ ሕገ-ወጥ እርምጃዎች ሙሉ ተባባሪ በመሆን፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አቤቱታዎች አላዳምጥ በማለት ለከፍተኛ ጉዳት የዳረገውን ተቋም ከኃላፊነት ነፃ ለማውጣት የተፈለገ ምስክርነት የሚመስል በመስጠቱ ቡድኑ መሰረታዊ ስሕተት ሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ሕዝብ 80 ከመቶ በላይ የሆነው ሊጠቀምበት የሚገባውን የሴፍቲኔት (Safety net) ለአባላት ምልመላና የድምጽ መሸመቻ አድርጎ ኢህአዴግ መጠቀሙ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ እያለ ይህንን በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን በደል መታዘብ ያለመቻሉ አስገራሚ ነው፡፡

እንደዚሁም የግንቦት 2002 ምርጫን በከፍተኛ ደረጃ ተዓማኒነት ካሳጡት የኢህአዴግ ሕገ-ወጥ እርምጃዎች መካከል ዋነኛ የነበረውን 1 ለ5 ጥርነፋና በቡድን ድምጽ የመስጠት ቅንጅትና ለዚህም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሁኔታዎችን እዳመቻቸ ቡድኑ ሳይታዛብ መቅረቱ ወይም ታዝቦትም በሪፖርቱ ያለማካተቱ ትልቅ ጉድለት መሆኑን መድረክ ተገንዝቦታል፡፡ በተጨማሪም የምርጫው ድምጽ መስጫ አንድ ቀን ብቻ ሲቀረው ‹መድረክ ከምርጫው ወጥቻለሁ አለ› የሚል የተጭበረበረ ሰነድ በኢህአዴግ ካድሬዎች ተዘጋጅቶ ስለመሰራጨቱ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መረጃ ደርሶትና መድረክም በጉዳዩ ላይ ማስተባበያ በመስጠት ይኸው በመገናኛ ብዙሃን እንዲገለጽ ምርጫ ቦርድ ተጠይቆ ከጉዳይ ያለመቁጠሩን፣ የአውሮፓ ታዛቢ ቡድን ይህንኑ በወቅቱ እንዲያውቀው መደረጉ ቢታወቅም፣ ይህንንም እንደጥፋት ወስዶ በሪፖርቱ ባለማካተቱ ተጨማሪ ጉድለት አሳይቷል፡፡ ከሁሉም በላይ በምርጫው እንቅስቃሴ ወቅትና በድምጽ መስጫው እለት በመራጩ ሕዝብ ላይ ስለደረሰው ጥቃት፣ እንግልትና እስከሞት ድረስ ስለተከፈለው መስዋእትነት በሪፖርቱ ያለመጠቀሱ ትልቅ ጉድለት እንደሆነ መድረክ አጢኖታል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ የአውሮፓ ህብረት የምርጫ 2002 ታዛቢ ቡድን ያወጣው የመጨረሻው ሪፖርት ገሀድ ያደረጋቸው ጉድለቶች መድረክ ስለ ምርጫው ለያዘው አቋም ተጨማሪ ማረጋገጫ ናቸው፡፡ ከታዛቢው ቡድኑ በጉድለትነት ከቀረቡት ክስተቶች መሀከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

1. የተካሄደው ምርጫ ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ ምርጫዎችን ለማካሄድ የገባቸውን ግዴታ ያላሟላት መሆኑን ያሳየ መሆኑ፣

2. የምርጫ ሂደቱ ግልጽነት ማጣቱና ለሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የተደላደለ የውድድር ምህዳር እንዳይኖር መደረጉ ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለውን አጀንዳ እውን ለማድረግ ከያዘው እቅዱ የመነጨ ሊሆን እንደሚችል፣

3. የምርጫው ሂደት መድልኦ የበዛበትና ነፃ መብቶች ማለትም፣ ነፃ እንቅስቃሴዎች፣ ስብሰባዎችና ሃሳብን በነፃነት መግለጽ ያልተከበረበት መሆኑ፣

4. ሀገራዊ ባለድረሻ አካላት ተገቢ ባልሆኑ ሕጎች ማለትም የማስሚዲያ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጆች ምክንያት በምርጫ ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸው የታቀበ መሆኑ፣

5. የአካባቢ አስተዳደሩ፣ የፖሊስና የደህንነት አካላት ለገዢው ፓርቲ በመወገን በተቃዋሚ ድርጅቶች የምረጡኝ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ማሳረፋቸው፣

6. የመንግሥት፣ የሕዝብ ሀብት ለገዢው ፓርቲ ምርጫ ቅስቀሳ መዋሉ፣

7. በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን ለገዢው ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ከማድረግ አልፈው የተመጣጠነ ዘገባ ያለማቅረባቸው፣

8. የተቃዋሚ ፓርቲዎች እጩ ተወዳዳሪዎች ላይ በመንግሥት የሚወስዱት የበቀል እርምጃዎች ስጋት የሰፋ መሆኑ፣

9. ምርጫው የተካሄደው ባልተሟላ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ዝርዝር ላይ ተመስርቶ መሆኑና የመራጮች ምዝገባ ሰነድ ተዓማኒነት አጠራጣሪ መሆኑ፣

10. ታዛቢው ቡድን በናሙናነት ከገመገማቸው ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ27 ከመቶው በተቆጠረው ድምጽና በውጤትነት በተመዘገበው አሃዝ መካከል ልዩት መኖሩ ምርጫው በስፋት ለመጭበርበሩ ጠቋሚ መሆኑ፣

11. በታዛቢው ቡድን በተቃኙባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ በሚሆኑት ላይ የድምጽ ቆጠራው ውጤት ያለመለጠፉ እና 25 ከመቶ በሚሆኑቱ ደግሞ ለተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪዎች የቆጠራው ውጤት የተሞላበት ፎርም ያለመስጠቱ፣ በድምጽ ቆጠራው ወቅት ማጭበርበር ስለመኖሩ አመልካች መሆኑ ናቸው።

እንግዲህ ኢህአዴግና መንግሥቱ ምርጫውን ለመታዘብ ፈልገው ከነበሩት የውጭ አካላት መካከል በገለልተኛነቱ እምነት ኖሮዋቸው ፈቃድ የሰጡት የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢ ቡድን ስለምርጫው ስለምርጫው ‹ያየሁትና የተገነዘብኩት ይህ ነው› ብሎ ያቀረበውን ሪፖርት ‹ፍፁም ቅጥፈትና የፖለቲካ አጀንዳ ያለው ሥራ ነው ወዘተ› ብሎ ጥላሸት ለመቀባት መሞከሩና ሪፖርቱም በሀገር ውስጥ እንዳይቀርብ መከልከሉ፣ የመጀመሪያው አይደለም፣ የ1997 ዓም ምርጫ ታዛቢ በነበረውና በአና ጎሜዝ በተመራው የአውሮፓ ሕዝበረት ቡድን ላይም ከአንድ መንግሥትና ሕዝብ እመራለሁ ከሚል ፓርቲ የማይጠበቅ ተራ ዘለፋ ሲካሄድ ከርሟል።

ለነገሩማ ኢህአዴግን ‹ሁሉንም ጉዳይ ለብቻዬ ልቆጣጠር› የሚለው አባዜው ተጠናውቶት እንደ አንድ ገለልተኛ ተብሎ ትናንት የተቀበሉት አካል ከሁሉም በምርጫው ተፎካካሪ ወገኖች ምኞትና ፍላጎት የወጣ ሪፖርት ካየውና ከተገነዘበው በመነሳት ማቅረብ እንደሚችል የታወቀ ነው። ስለሆነም በመድረክ እምነት የፈለገው ያህል የኢህአዴግ

ጨኸትም ሆነ ውግዘት በአወሮፓ ሕብረት ታዛቢ ቡድኑ ሪፖርት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፣ የሪፖርቱንም ፋይዳ አይቀንሰውም፡፡ ትርፉ ግን ትዝብት ብቻ ነው!

መድረክ የ2002 ዓም ምርጫ ውጤት ኢህአዴግ በዘረፋ የወሰደው ምርኮ ስለመሆኑ አቋም በመወሰዱና ውጤቱንም በመቃወሙ ከኢህአዴግና አጋሮቹ ከሥነ-ምግባር የወጣ ዘለፋና ስም ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር የአውሮፓ ሕብረቱ ሪፖርት መድረክ ስለ ምርጫው ሂደትና ውጤት ያለውን አቋም በማረጋገጥ ረገድ ረዥም መንገድ የሄደ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ የምርጫውን ሂደትና ውጤት በሚመለከት ማን እየዋሸና በሕዝብ መብትና የሥልጣን ባለቤትነት ክቡር ጉዳይ ላይ ማን እያሾፈ እንደሆነ መላው ሕዝባችንና ዴሞክራቱ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ተዓማኒ ምስክርነት አግኝቷል የሚል እምነት ይኖረናል፡፡

ከዚህም በመነሳት መድረክ ከመነሻው አቋሙ በመጽናት አሁንም የግንቦት 2002 ዓም ምርጫ ተብዬው ተውኔት ውጤት የምንቃወመው መሆኑ ታውቆ፣ ነፃ፣ ፍትሓዊና ተዓማኒ ምርጫ ይካሄድ ይላል፡፡ ይህም እውን እንዲሆን ከዚህ ቀደም ጳግሜ 4 ቀን 2002 ዓም በዝርዝር ባስቀመጣቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ኢህአዴግ ከመድረክና ሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር መደራደርና መነጋገር ይኖርበታል፡፡ መላው የሥልጣን ባለቤትነቱን በግንቦት 2002 ምርጫ የተቀማው ሕዝባችንም ከአውሮፓ ሕብረት ታዛቢ ቡድን በቀረበው ሪፖርት በመደፋፈር በሀገራችን ነፃ፣ ፍትሓዊና ተዓማኒ ምርጫ የሚካሄድበትን ሁኔታ እውን ለማድረግ ተያይዞት ያለውን ሠላማዊ ትግል ከምን ጊዜውም በላይ እንዲያፋፍም ጥሪ እናደርጋለን፡፡

ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚደረገው ትግል ግቡን ይመታል!

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓም

<u>አዲስ አበባ</u>